# <u>አስጨናቂውን ዘመን በክርስቶስ መስቀል ኃይል እንሻገር!</u>

**2 <u>ጢሞቴዎስ 3፡1-5 ፤ 2 ጴጥሮስ 1፡3-4</u>**

## I. <u>አስጨናቂውና የመጨረሻው ዘመን ባህርያት (2 ጢሞቴዎ 3፡1-5)</u>

በዘመናችን ኢየሱስን እንዳመኑ የሚናገሩ፣ ወደ ጸሎትና አምልኮ ስፍራዎች የሚመጡ፣ በተለያዩ ዘርፎች እናገለግላለን የሚሉ፣ መንፈሳዊ ቋንቋ መናገር በጣም የሚችሉ፣ ወዘተ ነገር ግን በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው በእግዚአብሔር መጠራታቸውንና መመረጣቸውን በሚኖሩት ተጨባጭ ክርስቲያናዊ ሕይወት የማያስመሰክሩ ብዙዎች ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ከመጨረሻው ዘመን ምልክቶች ዋነኛው ነው፡፡ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡-

> *ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ፡፡ (2 ጢሞቴዎስስ 3፡1)*

ይህ ጳውሎስ ***"መጨረሻው ዘመን"*** ብሎ የጠቀሰው ጊዜ በአንደኛው ምዕተ ዓመት እና በክርስቶስ ዳግም ምጽአት መካከል ያለውን ጊዜ የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ ጊዜ በአጠቃላይ በሕብረተሰቡ ዘንድ እነደዚሁም በቤተ ክርስቲያን ዙርያ በሚገኙ ሰዎች ዘንድ ሞራላዊ ውድቀት የሚታይበት አስከፊ ጊዜ እንደሆነ ጳውሎስ አስረድቷል፡፡ ይህንን እውነት በግልጽ ለማስረዳት ጳውሎስ ከቁጥር 2-5 ድረስ ባለው ክፍል በጣም አስገራሚ የሆኑ 19 አጠቃላይ ባህርያትን ዘርዝሯል፡፡

*<u>ሰዎች እንዲህ ይሆናሉ፡-</u>*

1) ***ራሳቸውን የሚወዱ፡-*** ራሳቸውን ብቻ ማዕከል ያደረገ ሕይወት የሚኖሩ ይሆናሉ፡፡ የአስተሳሰባቸው፣ የስሜታቸው፣ የፈቃዳቸውና የድርጊታቸው ማዕከል ወይም መካከለኛ <u>"እኔ"</u> የሚለው ቃል ነው፡፡ ንግግራቸው ሁሉ እኔ፣ ለእኔ፣ የእኔ፣ … በሚሉት ቃላት የተሞሉ ናቸው፡፡ ይህ እኔነት ደግሞ የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው፡፡
2) ***ገንዘብን የሚወዱ፡-*** ገንዘብ አምላካቸው የሆነባቸው፣ ከእግዚአብሔር ፍቅር ይልቅ የገንዘብ ፍቅር የተጠናወታቸው ይሆናሉ፡፡ ገንዘብን መውደድ ደግሞ የክፋት ሁሉ ሥር ስለሆነ ከገንዘብ ምኞት የተነሳ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ይወጋሉ፡፡ (1 ጢሞቴዎስ 6፡10)
3) ***ትምክህተኞች፡-*** ያለ እኔ ማንም የለም የሚል አመለካከት ያላቸውና ራሳቸውን በማስተዋወቅ የተጠመዱ ናቸው፡፡ ትምክህት የሰዎችን የውስጥ ማንነት ይገልጻል፡፡
4) ***ትዕቢተኞች፡-*** ከመጠን በላይ ግትሮች፤ እኔ ብቻ ትክክለኛ ነኝ፤ እኔ ብቻ አዋቂ ነኝ የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ብዙ ጊዜ የራሳቸውን ጥቅም የሚያሳድዱ ናቸው፡፡
5) ***ተሳዳቢዎች፡-*** ለሌሎች ፈጽሞ አክብሮት የሌላቸው፣ ስነ-ምግባር የሌላቸውና ሌሎችን የሚያዋርዱ ናቸው፡፡
6) ***ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፡*** - እናትና አባታቸውን የማያከብሩና ልባቸው ባለመታዘዝ የተሞላ፤ እምቢተኞች ይሆናሉ፡፡
7) ***የማያመሰግኑ፡-*** እግዚአብሔር ያደረገላቸውን የማያስተውሉ፡፡ ምንም ቢደረግላቸው የምስጋና አንደበት የሌላቸው፣ ሁልጊዜ እንዳልተደረገላቸው ሰዎች የሚኖሩ ናቸው፡፡
8) ***ቅድስና የሌላቸው፡-*** የጽድቅ፣ የንስሐና በክርስቶስ ደም የመንጻት ሕይወት የማይኖሩ፡፡
9) ***ፍቅር የሌላቸው፡-*** ለሌሎች መልካምነትና በጎነት ራሳቸውን የማይሰጡ፣ ልባቸው የተዘጋና ርህራኄ አልባ ይሆናሉ፡፡

10) ***ዕርቅን የማይሰሙ፡-*** ለዕርቅ ልባቸው ፈጽሞ የማይከፈት፣ ክርስቶስ ያደረገላቸውን ይቅርታና የኃጢአት ስርየት ፈጽመው የዘነጉ ይሆናሉ።

11) ***ሐሜተኞች፡-*** ለጸሎት፣ ቃሉን ለማንበብና ለወንድማማች ፍቅር ጊዜ የሌላቸው ነገር ግን የሰዎችን ስምና ማንነት ለማጥፋት የሚተጉና ጊዜያቸውን የሚሰጡ።

12) ***ራሳቸውን የማይገዙ፡-*** ለሥጋ አምሮትና ምኞት እንደዚሁም ዓለም ለምታቀርበው የኃጢአት ግብዣ እምቢ ማለት የማይችሉ።

13) ***ጨካኞች፡-*** ያሰቡት ነገር ይከናወን እንጂ ሌላውን ረግጦና ጨፍልቆ ከመሄድ የማይመለሱ። (<u>አባባል፡-</u> *በፍየል ዘመን እንደ በግ አትኑር!)*

14) ***መልካም የሆነውን የማይወዱ፡-*** ከየውኃት፣ ከቅንነትና ከበጎነት መንፈስ ይልቅ ክፋት፣ ተንኮልና ጠማማነትን የሚወዱና የሚከተሉ።

15) ***ከዳተኞች፡-*** በቃላቸውና በንግግራቸው ፈጽመው የማይገኙ፣ ቃላቸውን ፊት ለፊት በግልጽ የሚሽመጥጡ፣ የገቡትን ስምምነት ያለ ምንም ይሉኝታ የሚያፈርሱ። በእነዚህ ሰዎች ውስጥ እውነተኛነትና ታማኝነት አይገኝም።

16) ***ችኩሎች፡-*** ተረጋግተው የእግዚአብሔርን ሃሳብና ፈቃድ ለማስተናገድ የማይችሉ፣ በገዛ ፈቃዳቸው የሚሮጡ ናቸው። እነዚህ ሰዎች የሚሰሩትና የሚያደርጉት ነገር የሚመሰረተው ጊዜ በማይሽረውና ከፍ ባለው በእግዚአብሔር ሰማያዊ መመርያ (በእግዚአብሔር ቃል) ላይ ሳይሆን በወቅታዊ ሁኔታ በመነዳት ነው። ስለዚህ ማንነታቸው በሰማያዊ መመርያ የተቃኘ ስላልሆነ ሁልጊዜ የሚለዋወጡ ናቸው።

17) ***በትዕቢት የተነፉ፡-*** እነዚህ ራሳቸውን ከመጠን በላይ የሚክቡ፣ ሌሎችን የሚንቁና ቁልቁል ወደታች የሚመለከቱ ናቸው።

18) ***ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፡-*** ከሰማያዊውና ከዘላማዊው ነገር ይልቅ ለጊዜው በኃጢአት ለሚገኝ ደስታ ራሳቸውን የሚሰጡ፣ ምቾታቸውን ብቻ የሚያስጠብቁ ናቸው። እግዚአብሔርን አጥብቆ ከመፈለግ ይልቅ ተድላንና ቅንጦትን የሚወዱና የሚያሳድዱ ናቸው።

ለእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ስለ ሙሴ በዕብራውያን 11፡25-26 "ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤ ብድራቱን ትኵር ብሎ ተመልክቶአልና።" ተብሎ የተጻፈው ቃል ፈጽሞ አይዋጥላቸውም፣ አይቀበሉትምም።

19) ***የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፡-*** እነዚህ አስመሳዮች ናቸው። ከውጭ ለሰዎች የሚታዩ መንፈሳዊ የሚመስሉ ነገሮችን የሚያከናውኑ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ኃይል የካዱ ሰዎች ናቸው። እነዚህ እንደ ፈሪሳውያን ግብዞች ናቸው። ኢየሱስ ስለ ግብዞች ሲናገር እንዲህ ብሏል፡-

*እናንተ ግብዞች፥ ኢሳይያስ ስለ እናንተ። ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፥ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤ የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ብሎ በእውነት ትንቢት ተናገረ። (ማቴዎስ 23፡7-9)*

*እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጡ ግን የሙታን አጥንት ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ፥ ወዮላችሁ። እንዲሁ እናንተ ደግሞ በውጭ ለሰው እንደ ጻድቃን ትታያላችሁ፥ በውስጣችሁ ግን ግብዝነትና ዓመፀኝነት ሞልቶባችኋል። (ማቴዎስ 23፡27-28)*

በጣም አስደንጋጭ የሚሆነው ግን እነዚህ በ2 ጢሞቴዎስ 3፡1-5 የተዘረዘሩት ባህርያት አማኞች ነን በሚሉ ሰዎች መካከል ስላለው ሁኔታ ጭምር የሚናገሩ መሆናቸው ነው፡፡ ይህን ለማረጋገጥ ከቁጥር 5 በኋላ ያለውን ክፍል በግል ማንበብ ይቻላል፡፡ አሁንም በዘመናችን እንዲህ ዓይነት ሰዎች በምድር ባለችው በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ዙርያ ይገኛሉ፡፡ ለዚህ ነው ጳውሎስ፡- "***ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ***" በማለት ለጢሞቴዎስ በግልጽ የጻፈለት፡፡

ይህ ዘመን ለቤተ ክርስቲያን፣ በክርስቶስ ፍጹም የሆነ ሰው ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ለሚደክሙ አገልጋዮች፣ ለእውነተኛ አማኞች፣ ለቅዱሳን ጉባኤ፣ ቤተ ክርስቲያን ብርሃንነትዋና ጨውነትዋ እንዲገለጥ ለሚፈልጉ፣ የክርስቶስ መልክና ውበት በቤተ ክርስቲያን እንዲታይና በዓለም ተጽዕኖ እንዲያመጣ ለሚፈልጉ፣ ወዘተ አስጨናቂ ጊዜ ነው፡፡ ዋነኛው ምክንያቱ ደግሞ "***የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤" (ቁ. 5)*** የሚለው እውነት ነው፡፡

ይህ ዘመን የሚያስጨንቅ ዘመን የሆነው የአምልኮ መልክ ያላቸው ነገር ግን የእግዚአብሔርን ኃይል የካዱ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን መብዛታቸው ነው፡፡ የአምልኮ ስርዓቱን ያውቁታል፣ ዝማሬ ይችላሉ፣ መንፈሳዊ ቃላት መናገር ይችሉበታል፣ ወዘተ ነገር ግን ሕይወታቸው በተግባር ሲፈተሽ ዓለማዊነትና ስጋዊነት የተጠናወታቸው፣ መንፈሳዊ ፍሬ የማይታይባቸውና መንፈሳዊ እሴትንና ሰማያዊ የኑሮ ዘይቤን ጥለው በምድራዊ እሴትና ዓለማዊ የኑሮ ዘይቤ የሚመላለሱ ናቸው፡፡ ይህንን ስንመለከት እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሰዎችን የመለወጥ ኃይል ፈጽሞ የካዱ ናቸው፡፡ ለዚህ ነው ጳውሎስ "**የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል**" በማለት የተናገረው፡፡

እኛ ራሳችንን በእግዚአብሔር ቃል ስንመዝን ምን እንመስል ይሆን? የአምልኮ መልክ የተላበስን ነገር ግን የእግዚአብሔርን ኃይል የካድን እንሆን ወይስ የእግዚአብሔርን ለዋጭ ኃይል እየተለማመድን ከዚህ ኃጢአተኛ ዓለም ክፋትና ርኩሰት በላይ እየኖርን በዚህ የመጨረሻውና አስጨናቂ ዘመን የክርስቶስ ምስክሮች ሆነን እየኖርን ነው?

## II. <u>በክርስቶስ መስቀል ኃይል ዘመኑን መሻገር ይቻላል (2 ጴጥሮስ 1፡3-4)</u>

ታዲያ በዚህ አስጨናቂ በተባለው ዘመን እንደ እግዚአብሔር ሀሳብ እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትን ሕይወት መኖር የምንችለው እንዴት ነው፡፡ የዚህ መልስ አጭር ነው፡- ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሰራው ስራ የተነሳ ለእኛ የተደረገልንን ነገርና የተለቀቀልንን ግብዓት (ሪሶርስ) በሚገባ ማወቅና እነዚህን በመለማመድ ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዛሬ ሦስት መሰረታዊ ነገሮችን ልናገር እወዳለሁ፡፡

### 1) <u>በክርስቶስ የመስቀል ስራ ከመለኮት ኃይል ተካፋዮች ሆነናል (2 ጴጥሮስ 1፡3)</u>

*በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኃይል ሰጥቶናል፡፡ (2 ጴጥሮስ 1፡3)*

ይህ ከክርስቶስ የተቀበልነው ሰማያዊ ሕይወት ከእግዚአብሔር የተቀበልነው እንደመሆኑ መጠን መለኮታዊ ባህርይ አለው፡፡ ይህንን ሕይወት በራሳችን ልንኖረው አንችልም፡፡ ከዚህ የተነሳ ክርስቶስ ከሙታን በመነሳት በክብር ካረገ በኋላ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ አፈሰሰልን፡፡

*"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ።" (ሐዋ 1፡8)*

ይህ አማኞች ከመንፈስ ቅዱስ የሚቀበሉት መለኮታዊ ኃይል ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያስፈልጋቸውን ማንኛውንም ጉልበት ይሰጣቸዋል። መለኮታዊ ሕይወትን ለመኖር መለኮታዊ ኃይል፣ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል፣ የክርስቶስን ኃይል ተቀብለናል። የመለኮታዊ ኃይል ምንጭ ደግሞ የሚገኘው ክርስቶስንና በመስቀል ላይ የሰራውን ስራ በሚገባ በማወቅ ነው። የመለኮታዊ ኃይልና የመንፈሳዊ እድገት ምንጭ ክርስቶስን በሙላት ማወቅ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ኃይል መለማመድ በልሳን ከመናገርና በአገልግሎት የጸጋ ስጦታዎቻችንን ከመግለጥ በላይ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ኃይል መለማመድ በግል ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የግል ሕብረትና ግንኙነት በጠበቀ መልክ ማድረግ ነው። መስጠት ነው። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የጠበቀ የግል ሕብረት ያላቸውና ከመለኮት ኃይል ተካፋዮች መሆናቸውን በማወቅ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚመላለሱ አማኞች ይህንን አስጨናቂ ዘመን ይሻገራሉ።

2) <u>በክርስቶስ የመስቀል ስራ የመለኮት ተስፋ ተካፋዮች ሆነናል (2 ጴጥሮስ 1፡4ለ)</u>

*በእነዚህ ነገሮች አማካይነት እጅግ ታላቅና ክቡር የሆነውን ተስፋ ሰጥቶናል። (2 ጴጥሮስ 1፡4ለ)*

ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሰራው ስራ፤ ከክብሩና ከበጎነቱ የተነሳ የከበረና ውድ የሆነ መለኮታዊ ተስፋ ሰጥቶናል። ይህ ተስፋ ደግሞ እጅግ ታላቅና ክቡር እንደሆነ ጴጥሮስ በግልጽ ተናግሯል።

<u>የአዲስ ልደት ተስፋ፡-</u>

*እርሱ (እግዚአብሔር) ከታላቅ ምህረቱ የተነሳ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሳት ምክንያት ለሕያው ተስፋ በሚሆን አዲስ ልደት ... ወለደን። (1 ጴጥሮስ 1፡3)*

<u>በእግዚአብሔር ኃይል የመጠበቅ ተስፋ፡-</u>

*እናንተም በመጨረሻው ዘመን ሊገለጥ የተዘጋጀው ድነት እስኪመጣ ድረስ በእምነት አማካይነት በእግዚአብሔር ኃይል ተጠብቃችኋል። (1 ጴጥሮስ 1፡5)*

<u>የእግዚአብሔር የማስቻል ኃይል ተስፋ፡-</u>

*በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኃይል ሰጥቶናል። (2 ጴጥሮስ 1፡3)*

<u>የዘላለም ሕይወት ተስፋ</u>

*ያን መንፈስም፥ በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን፥ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው። (ቲቶ 3፡6-7)*

<u>የሚመጣውን ዓለም የመውረስ ተስፋ</u>

*እኛ ግን ጽድቅ የሚኖርበትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በተስፋ ቃሉ መሰረት እንጠባበቃለን። (2 ጴጥሮስ 3፡13)*

የመለኮት ተስፋ ተካፋዮች መሆናቸውን በማወቅ እግዚአብሔር በሰጣቸው ተስፋ በመታመን የሚኖሩ አማኞች ይህንን አስጨናቂ ዘመን ይሻገራሉ።

3) <u>በክርስቶስ የመስቀል ስራ ከመለኮት ባህርይ ተካፋዮች ሆነናል (2 ጴጥሮስ 1፡4ሀ)</u>
*ከክፉ ምኞት የተነሳ በዓለም ካለው ምግባረ ብልሹ ሕይወት አምልጣችሁ ከመለኮት ባህርይ ተካፋዮች እንድትሆኑ፤ (2 ጴጥሮስ 1፡4ሀ)*

ይህ ከላይ የጠቀስነው መለኮታዊ ተስፋ አማኞች የመለኮት ባህርይ ተካፋዮች እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፡፡ ይህ አማኞች የመለኮትን ተፈጥሮ ይወርሳሉ ለማለት ሳይሆን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእነርሱ ውስጥ ስለሚያድርና ስለሚኖር ወደ አማኞች የሚተላለፉ የእርሱን ባህርያት ይካፈላሉ ማለት ነው (<u>ለምሳሌ</u>፡- ጽድቅ፣ ቅድስና፣ ፍቅር፣ ወዘተ)፡፡ የመለኮታዊ ባህርይ ተካፋይ መሆን የሚያመለክተው ክርስቶስን መምሰል ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በሙላት በሕይወታችን መገለጡ ነው፡፡

አማኞች የእግዚአብሔር ባህርይ ተካፋዮች ከመሆናቸው የተነሳ በዚህ ኃጢአተኛ ዓለም ሲኖሩ ከአስመሳይነትና ከግብዝነት በመላቀቅ በኃጢአት ላይ ድል በመንሳትና በሞት ላይ ድል በመቀዳጀት መኖር ይችላሉ፡፡ ከተሰጣቸው የአዲስ ልደት ተስፋ፣ በእግዚአብሔር ኃይል የመጠበቅ ተስፋ፣ በእግዚአብሔር የማስቻል ኃይል ተስፋ፣ የዘላለም ሕይወት ተስፋ እና የሚመጣው ዓለም የመውረስ ተስፋ የተነሳ አማኞች ከመለኮታዊ ባህርይ ተካፋዮች መሆን ችለዋል፡፡ አማኞች የመለኮታዊ ባህርይ ተካፋዮች ስለሆኑ ከክፉ ምኞት የተነሳ በዓለም ካለው ምግባረ ብልሹ ሕይወት ማምለጥ ይችላሉ፡፡ ከመለኮት ባህርይ ተካፋዮች እንድንሆን ስለ ተጠራን ይህን አስጨናቂ ዘመን በድል መሻገር እንችላለን፡፡

ስለዚህ በዚህ የአምልኮት መልክ ያላቸው ኃይሉን ግን የካዱ ሰዎች በበዙበትና ከዚህም የተነሳ አስጨናቂ በሆነበት ዘመን ከግብዝነትና ከአስመሳይነት በመራቅ በመስቀል ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰራልንን ስራና ከእርሱም ስራ የተነሳ እኛ የተቀበልነውን ሰማያዊ ግብዓት (ሪሶርስ) በመረዳት እንደ ጥሪያችን እንኑር፡፡ እግዚአብሔር መለኮታዊ ኃይል ስለሰጠን፣ የመለኮታዊ ባህርይ ተካፋይ ስላደረገን እና የመለኮታዊ ተስፋ ወራሾች ስላደረገን የዚህን አስጨናቂ ዘመን ተግዳሮት ተቋቁመን በዚህ ኃጢአተኛ ዓለም በአሸናፊነት መኖር እንችላለን፡፡